# የአርበኞች ግንቦት ሰባት ምክትል ሊቀመንበርና የበረሀ ከፍተኛ አመራሮችና ኮማንደሮች አዲስ አበባ አለመገኘታቸው እያነጋገረ ነው ።

September 10, 2018

አርበኞች ግንባር ምን ሆነ? ( ጌታቸው ሽፈራው )

ታጋይ መዓዛው ጌጡ የአርበኞቹ ኃላፊ፣ ፕሮፌሰር ብርሃኑ የግንቦት 7 ሆነው ድርጅቶችን አዋህደዋል። በሂደት እንደ ድርጅት መንገጫገጭ ገጥሟቸው እንደነበር ተገልፆአል።

ዛሬ ደግሞ አንዳንድ ጥርጣሬዎች ተፈጥረዋል። ማዕዛው ጌጡ በድርጅቱ 2ኛ ሰው ነው። በታጋዩ ዘንድ ደግሞ ትልቅ ተቀባይነት አለው። ከዚህ ግባ የሚባል ሚና የሌላቸው ኤርትራ የነበሩ ሰዎች ከእነ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ጋር ሲታዩ ምክትል ሊቀመንበሩ/ የነበረው ማዕዛው ግን አልተገኘም።

ለወር ያህል በነበረው ቅስቀሳ ስለማእዛውና ሌሎች የአርበኞች ቁልፍ አመራሮች ቅስቀሳ ሲደረግ አልታየም። እነ ማዕዛውን ያህል ከፍተኛ አመራር ይቅርና በዛሬው ዝግጅት እንዲገኙ ከድርጅቱ ውጭ የሚገኙ ሌሎች ግለሰቦች ጥሪ ተደርጎላቸው ነበር። ለአብነት ያህል መገኘት ስላልቻሉ/ስላልፈለጉ እንጅ እነ ንግስት ይርጋ እና ኮ/ል ደመቀም ጭምር አዲስ አበባ እንዲገኙ ተጠርተው ነበር።

የድርጅቱ አባል ያልሆኑ ታዋቂ ሰዎች ሲጠሩ እነ ማዕዛው ለምን አልተገኙም? ማዕዛው ጌጡ ጎንደር እንደሚገኝ ተገልፆአል። የአርበኞች ግንቦት 7 አባል የነበረውና ታስሮ ከተፈታ በኋላ ዛሬ ከአዲሃን ጋር ወደሀገር የገባው ጋዜጠኛ ጉዳይም እንዲሁ የሚታይ አይደለም።

የአርበኞች ግንቦት 7 ምክትል የሆነው/የነበረው ማዕዛው ጌጡ አዲስ አበባ ከሚገኙት እነ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ይልቅ ዛሬ ጎንደር ከገቡት የአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ (አዲኃን) ሊቀመንበር መኪና አስቁሞ ሰላምታ ሲሰጠው ፎቶ ተነስቷል ተብሏል። ከአቶ ማዕዛው በተጨማሪ የአርበኞች ግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር የነበረውና ከድርጅቱ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ከድርጅቱ የወጣው ታጋይ ዘመነ ካሴ የአዲኃን ታጋዮችን ሁመራ ድረስ ሄዶ ተቀብሏል።



እን ክፈተው አሰፋን የመሰሉ የአርበኞች አመራሮችም አዲስ አበባ በነበረው ዝግጅት የተገኙ አይመስልም። ታጋይ ክፈታው አሰፋ ዛሬ የአርበኞችን የትግል መዝሙር በፌስቡክ ሲያስነብብ ውሏል።

በአርበኞቹ ሰፈር ምን ተፈጠረ?